የዐድዋ ፡ ዘላለማዊ ፡ ድል ፡ ባተራማሽና ፡ ባጥፊ ፡ ስያስ ፡ አይደብስም ።

ለንደን ፥ መጋቢት ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

በዓለም ፡ ደረጃ ፡ የተስፋፋውን ፡ እጅግ ፡ አደገኛውን ፡ የ"ኮሮና ፡ ተላላፊ" ፡ ወረርሽኝ ፡ ለማሸነፍ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታትና ፡ አህጉራውያን ፡ ተቋማት ፡ በሞላ፟ቸው ፡ በሚያስደንቅ ፡ መተባበርና ፡ መናበብ ፡ በሚታገሉበት ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፥ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የተንጠለጠለው ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ የሀገሪቱን ፡ ህልውና ፡ የሚፈታተን ፡ ባዕድ-መሯ፟ሽ ፡ ተልእኮውን ፡ መፈጸሙን ፡ ቀጥሏል ።

ኢትዮጵያ ፥ ቅኝ ፡ ገዢነትን ፡ ድል ፡ ባደረገችበት ፡ በየካቲት ፡ 23 ፡ ቀን ፡ 1888 ፡ ዓ.ም. ፡ የዐድዋ ፡ ጦርነት ፡ 124ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡ ሰሞን ፥ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ("የኢትዮጵያ ፡ ፌዴራላዊ ፡ ዴሞክራሲያዊ ፡ ሪፓብሊክ" ) ፡ የ"ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.-ብልጽግና ፡ ፓርቲ" ፡ የውንብድና ፡ ይዘት ፥ በሌለው ፡ ሥልጣንና ፡ የራሱን ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት" ፡ (አንቀጽ ፡ 5) ፡ በመጣስ ፥ "በጉባኤ ፡ አጽድቄያቸዋለኹ" ፡ ያላቸውን ፡ ኹለት ፡ አጥፊዎች ፡ የስያስ ፡ ሰነዶች ፡ ይፋ ፡ አውጥቷል ። በዚህ ፡ አደራረጉ ፥ ያፈጣጠሩን ፡ ዐይነት ፣ የተልእኮውን ፡ ምንነትና ፡ የላኪውን ፡ ማንነት ፡ ለዓለሙ ፡ ኹሉ ፡ ፍንትው ፡ አድርጎ ፡ ከሥ፞ቷል ።

እንደ ፡ መግቢያ ፡ የቀረበው ፡ የመዠመሪያው ፡ የስያስ ፡ ሰነድ ፥ በትረካው ፡ ፍጹም ፡ ንኀለተኛ ፡ ("ኒኂሊስት" ) ፡ የኾነውን ፡ ያኸል ፥ የኢትዮጵያ ፡ ተማሪዎች ፡ የሀገራቸውን ፡ ታሪክ ፡ በሀገራዊ ፡ ቋንቋቸው ፡ በዐማርኛ ፡ ከመማር ፡ ከልክሎ ፥ በእንግሊዝኛ ፡ እንዲማ፟ሩት ፡ ያስገድዳል ።

ኹለተኛውና ፡ ዋነኛው ፡ የስያስ ፡ ሰነድ ፡ ደግሞ ፥ ላንድ ፡ ሺሕ ፡ ዓመታት ፡ በአንድያ ፡ መንግሥታዊ ፡ ልሳንነት ፡ ያገለገለውን ፡ ዐማርኛ ፡ አካቴውን ፡ በማስወገድ ፥ በምትኩ ፡ 5 ፡ ደቫ፟ሎች ፡ የሥራ ፡ ቋንቋዎችን ፡ በ"ደቫ፟ዩ ፡ መንግሥት" ፡ ደረጃ ፡ በመመደድ ፥ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተፎካክረውና ፡ ተራኵተው ፡ የሚጣጣሉበትን ፡ ደበኛ ፡ የቋንቋ ፡ ስያስ ፡ አስተዋውቋል ።

የኹለቱም ፡ ስያሶች ፡ የጋራ ፡ ግብ ፥ ለዘለቄታው ፡ ዐማርኛ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በአፍሪቃ ፡ የሚኖረውን ፡ ቦታ ፡ በመንሣትና ፡ ተስፋውን ፡ በመቅጨት ፥ በምትኩ ፥ እንግሊዝኛን ፡ አንድያው ፡ ያካባቢው ፡ የሥራ ፡ ቋንቋ ፡ ለማድረግና ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነትን ፡ ለመደምሰስ ፡ ያለበ ፡ የ124 ፡ ዓመት ፡ ደባ ፡ ነው ።

ይህ ፡ በ"ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.-ብልጽግና ፡ ፓርቲ" ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ መሣሪያነት ፡ የሚፈጸም ፡ ፀረ ፡ ኢትዮጵያ ፣ ፀረ ፡ አፍሪቃ ፡ እና ፡ ፀረ ፡ ሥልጣኔ ፡ የምልክዮሽ ፡ (የ"ኢምፔሪያሊዝም" ) ፡ ኀይሎች ፡ ድርጊት ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላ፟ ፡ አፍሪቃ ፡ ላይ ፡ በተለየ ፡ መመጻደቅና ፡ ተንኰል ፡ የተቃጣ ፡ የጥፋት ፡ ድርጊት ፡ ነው ። መላ፟ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ባንድነት ፡ በመቃወም ፡ ያስወግደዋል ፡ ሲል ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.) ፡ ሙሉ ፡ እምነቱን ፡ ይገልጻል ። በዐድዋ ፡ ድል ፡ ነጻ ፡ ለወጣው ፡ ለመላ፟ው ፡ የአፍሪቃ ፡ የብስ ፡ ሕዝብም ፡ የሐራ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ የሐራነቱ ፡ ታሪክ ፥ የ"ዐም ፡ ሐራ" ፡ ልሳን ፡ ዐማርኛም ፡ የነጻነቱ ፡ ልሳን ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ መቼም ፡ ቢኾን ፡ መላ፟ው ፡ የአፍሪቃ ፡ ሕዝብ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጐን ፡ ይቆማል ፡ ሲል ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ያምናል ።

1 ፤ ደባው ።

የተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ ኹነቶች ፡ ("ዩናይትድ ፡ ስቴይትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ" ) ፥ በእግዝእት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የውስጥ ፡ ጕዳይ ፡ ጣልቃ ፡ በመግባት ፥ በግንቦት ፡ ወር ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ "ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.-ብልጽግና ፡ ፓርቲ" ን ፡ በውንብድና ፡ አገዛዝነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሥልጣን ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ አላግባብ ፡ ጕብ ፡ እንዲል ፡ አድርገውታል ። የውንብድና ፡ አገዛዙም ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ በተነገረው ፡ ዕገውጡ ፡ መመሪያ ፡ መሠረት ፥ "ዐዲስ ፡ የቋንቋ ፡ ፖሊሲ" ፡ በሚል ፡ ርእስ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሳይጠይቅና ፡ ሳይጠ፟የቅ ፥ ዐማርኛን ፡ ከሀገራዊ ፡ ልሳንነት ፡ አውርዶ ፡ በመንግሥት ፡ የሥራ ፡ ቋንቋነት ፡ መድቦታል ። በዚህም ፡ ድርጊቱ ፥ ላለፉት ፡ 29 ፡ ዓመታት ፡ ዐማርኛን ፡ ተከታትሎ ፡ ከማድከም ፡ ጋራ ፥ ለእንግሊዝኛ ፡ ርምምድ ፡ በሩን ፡ በሰፊው ፡ ከፍቶ ፡ የግብር ፡ ከፋዩን ፡ ሕዝብ ፡ ገንዘብ ፡ ለዚህኛው ፡ ባዕድ ፡ ቋንቋ ፡ መስፋፊያ ፡ ሲያፈሰው ፡ ቈይቷል ።